## ክፍል የአንደኛ ሴሚስተር አካባቢ ሳይንስ ሞደል ፈተና

የጥያቄ ብዛት 40

የተፈቀደው ሰዓት 50 ደቂቃ

አጠቃላይ መመሪያ

ይህ የጥያቄ ወረቀት በውስጡ የ6ኛ ክፊል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ በአጠቃላይ አርባ (40) የምረጫ ጥያቄዎች አሉ፡፡ እያንዳንዱን ጥያቄዎች በጥናቃቄ በማንበብ በተሰጠው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ መልሱ የያዘውን ሆሄ (ፊደል) ባቻ በእረሳስ በመጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም በመልስ መስጫው ላይ የሚሞሉ መረጃዎችን በጥንቃቄ መሙላት ይገባል፡፡

ጥያቄውን ለማጠናቀቅ 50 ደቂቃዎች ተሰተዋል ልክ የተሰጠው ደቂቃ ሲያበቃ ወዲወኑ ጥያቄ መስራትን በማቆም አርሳስን በማስቀመጥ ሌላ ትእዛዝ አስኪሰጥ መጠበቅ የገባል፡፡

ማንኛውም አይነት ኩረጃ እና ለመኮረጅ መሞከር በቀጥታ ከፈተነው የሚያሰርዝ እና በህግ የሚያስጠይቅ መሆንን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የመልስ መስጫ ወረቀቱን ከመመለሱ በፊት ሁሉም አሰፈላጊ መረጃዎች እና ሁልም ጥያቄዎች መሰራታቸውን እርግጠኛ መሆን ይገባል፡፡

ጥር 2018 ዓ/ም

**ትዕዛዝ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በደንብ ካነበባችሁ በኋላ ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱን በመልስ መስጫው ላይ አስቀምጡ**

LIVEWORKSHEETS

1. ከሚከተሉት ውስጥ የአንድን አካባቢ መገኛ ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሰራሽ ነገሮች ጋር በማነፃጸር የሚገልፅ የትኛው ነው?

ሀ. የኬክሮስ መገኛ ለ. አንፃራዊ መገኛ ሐ. ፍጹማዊ መገኛ መ. የኬንትሮስ መገኛ

2. ከሚከተሉት ሀገራት ውስጥ ኢትዮጲያን በስተ-ደቡብምስራቅ የሚያዋስናት ሀገር የቱ ነው?

ሀ. ኤርትራ ለ. ጂቡቲ ሐ. ሶማሊያ መ. ኬንያ

3. ከሚከተሉት ውስጥ የአክሱም ሀውል ፍጹማዊ መገኛ በስተ ሰሜን ስንት ዲግሪ ኬክሮስ ላይ ነው?

ሀ. $22^0$ 25 58 ሰሜን ለ. $3^0$ ሰሜን

ሐ. $14^0$ 7 48 ሰሜን መ. $33^0$ ሰሜን

4. ከሚከተሉት ሀይቆች ውስጥ በሰሜን ኢትዮጲያ የሚገኘው የቱ ነው?

ሀ. ጣና ለ. ላንጋኖ ሐ. ሐዋሳ መ. ዝዋይ

5. ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ የጎግል ካርታ ጥቅም <u>**ያልሆነው**</u> የቱ ነው;

ሀ. ከሳተላይት ላይ ምስል ለመውሰድ ለ. የአየር ላይ ፎቶ ግራፍ ለማንሳት

ሐ. የገበያ ትስስር ለመፍጠር መ. መረጃን ለማከማቸት

6. ከሚከተሉተቱ ውስጥ ሃይድሮክሎሪክ አሲድ የሚይዘው ስረኣትልመት አካል ክፍል የቱ ነው?

ሀ. ትንሹ አንጀት ለ. አፍ ሐ. ጨጓራ መ. ትልቁ አንጀት

7. ከሚከተሉት ውስጥ ድብልቅ የሆነው ልዩቁስ የቱ?

ሀ. ወርቅ ለ. ካርቦን ዳይኦክሳይድ ሐ. ውሃ መ. የጨው ሙሙት



LIVEWORKSHEETS

8. ከሚከተሉት ውስጥ ከአንድ አይነት ንጥረ-ነገር ብቻ ወይም ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ ንጥረ-ነገሮች በሚያካሄዱት ኬሚካዊ ለውጥ የሚፈጠር ልዩ ቁሶች የትኛው ነው?

ሀ. ዋህድ-ዘር ድብልቆች　　ለ. ልይ-ዘር ድብልቆች

ሐ. ድብልቆች እና ውህዶች　　መ. ንፁህ ቁሶች

9. ከሚከተሉት የውህድ አይነቶች ውስጥ ቆምጣጣ ባህሪው ያለው የቱ ነው?

ሀ. ኦክሳይድ　　ለ. አሲድ　　ሐ. ቤዝ　　መ. ጨው

10. የአካባቢ ሳይንስመጽሐፍ ርዝመት 5ሳ.ሜ: ወርድ2ሳ.ሜ እናቁመት 6ሳ.ሜ ቢሆን ይዘቱ ስንት ነው?

ሀ. 7ሳ.ሜ$^3$　　ለ. 13ሳ.ሜ$^3$　　ሐ. 60ሳ.ሜ$^3$　　መ. 20ሳ.ሜ$^3$

11. ከሚከተሉት ውስጥ ለመኪናዎች፣ ለአውሮፕላኖች፣ ለመርከቦች፣ እና ለፋብሪካዎች ማንቀሳቀሻ የሚያስፈልገውን የሙቀት ጉልበት የሚያስገኘው የቱ ነው?

ሀ. የድንጋይ ከሰል　　ለ. ነዳጅ　　ሐ. ውሀ　　መ. ፀሀይ

12. ከሚከተለት ውስጥ ድምፅ በፍጥነት የሚተላለፈው በየትኛው ነው?

ሀ. አየር　　ለ. ውሃ　　ሐ. ወና　　መ. ብረት

13. ከሚከተሉት ውስጥ በኢትዮጲያ ከፍተኛ የዝናብ መጠን የሚመዘገብበት ቦታ የቱ ነው?

ሀ. ራስ ደጀን　　ለ. ዳሎል　　ሐ. አዋሽ ሸለቆ　　መ. ኦጋዴን



LIVEWORKSHEETS

14. ከሚከተሉት ውስጥ በአንድ ቦታ የሚሰተዋል ለረጅም ዘመነት የሚቆይ ቢያንስ ለሰላሳ(30)ዓመታት አመካኝ  የአየር ፀባይ የሚመዘገብበት የቱ ነው?

ሀ. የአየር ንብረትይዘት                    ለ. የአየር ንብረት

ሐ. የአየር ንብረት ተቆጣጣሪ                    መ. የአየር ሁኔታ

15. ከተሰጡ አማራጮች ውስጥ የአየር ንብረት ተቆጣጣሪ **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. ኬክሮስ        ለ. ከፍታ        ሐ. ሙቀት        መ. ቀላይ ሞገድ

16. ከሚከተሉት ውስጥ የማይታደስ የተፈጥሮ ሀብት የቱ ነው?

ሀ. የፀሀይ ብርሀን        ለ. ውሀ        ሐ. ዕፅዋት        መ. ነዳጅ

17. ከሚከተሉት ውስጥ በካርታ ወይም በሉል ላይ ስለሚገኙ አግድም መስመሮች ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ከሰሜን ወደ ደቡብ ይሰመራሉ                    ለ. ብዛታቸው 360 ነው

ሐ. ሁሉም መስመሮች ትይዩ ናቸው                    መ. መነሻ ($0^0$) ግሪንዊች ሜሪዲያን ይባላል

18. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካን በስተምሥራቅ የሚያዋስነው የቱ ነው?

ሀ. የኤደን ባህረ-ሰላጤ                    ለ. የኤርትራ ባህር

ሐ. መካከለኛው አፍሪካ                    መ. የህንድ ውቅያኖስ

19. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ ፍፁማዊ መገኛ የሚገልፅ የቱ ነው?

ሀ. ከ $18^0$ ሰሜን - $27^0$ ደቡብ ፣ ከ $22^0$ ምስራቅ - $51^0$ 28’ ምስራቅ

ለ. ከ $3^0$ ሰሜን - $15^0$ ሰሜን ፣ ከ $33^0$ ምስረቅ - $48^0$ ምስረቅ



LIVEWORKSHEETS


ሐ. ከ 30⁰ ሰሜን - 32⁰ ደቡብ ፣ ከ 22⁰ ምዕራብ - 22⁰ ምሥራቅ

መ. ከ 24⁰ ሰሜን - 27⁰ ሰሜን ፣ ከ 34⁰ ምዕራብ - 49⁰ ምዕራብ

20. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ አጎራባች ሀገር **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. ደቡብ አፍሪካ ለ. ዲሞክራቲክ ኮንጎ ሐ. ሰሜን ሱዳን መ. ግብፅ

**ጥያቄ ቁጥር 21 የሚከተለውን ምስዕል መሰረት አድረጋችሁ መልስ ስጡ**




21. ከላይ ካለው ምስል ቁጥር 5 ምንን ያመለክታል?

ሀ. ደም ቅዳን ለ. ደም መልስን

ሐ. ፑሉሞናሪ ቬን መ. ፑሉሞናሪ አርተሪ



LIVEWORKSHEETS

22. ከሚከተሉት ውስጥ በሽታ አምጪ ተዋስያንን ወይም ጀርሞችን በመከላከል የሰውነታችንን ጤንነት የሚጠብቅ የደም ህዋስ የቱ ነው?

ሀ. ነጭ የደም ህዋስ ለ. ቀይ የደም ህዋስ

ሐ. ፕላትሌት መ. ፕላዝማ

23. ከሚከተሉት ውስጥ በኦክስጂን የበለፀገ ደምን ወደ ሰውነታችን የሚረጨው የደም ክፍል የቱ ነው?

ሀ. ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ ለ. ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

ሐ. ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ መ. ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ

24. ከሚከተሉት ውስጥ የልብ ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ኦክስጂንለህብረ ህዋስ ማድረስ ለ. ደም መርጨት

ሐ. ደም ለማርጋት መ. ምግብን ለሕብረህዋስ ማድረስ

25. ከሚከተሉት ውስጥ በጉርምስኘና እነ በኮረዳነት ወቅት የሚከሰተው ተፈጥሯዊ ክስተት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የዳሌ መስፋት ለ. ክብደት አና ቁመት መጨመር

ሐ. የድምፅ መጎርነን መ. የትከሻ መስፋት

26. ከስረአት ትንፈሳ ክፍሎች ውስጥ አየር እና ምግብ በጋራ የሚተላለፍበት ክፍል የቱ ነው?

ሀ. ስርን ለ. ድህረ- አፍ ሐ. የአየርከረጢት መ. አፍ

27. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ድብልቅ ትክክል የሆነው የቱ ነው?



LIVEWORKSHEETS

ሀ. የሁለት እና ከዛ በላይ ልዩ ቁሶች አካለዊ ቅልቅል ውጤት ነው

ለ. ንፁህ ቁሶች የድብልቆች ምሳሌ መሆን ይችላሉ

ሐ. ድብልቆች እና ውህዶች አንድ አይነት ምንዝሮች አላቸው

መ. የሁለት እና ከዛ በላይ ንጥረ-ነገሮች ኬሚካዊ መስተጋብር ውጤት ነው

28. ከመሚከተሉት ውስጥ ጥቃቅን ቀዳዳዎች ባሉት እቃ በመጠቀም ፈሳሽ እና ያልሟሙ የጠጣር ድብልቅ የምንለይበት ዘዴ የቱ ነው?

ሀ. ንጥረት　　ለ.ቀረራ　　ሐ. ትነት　　መ.ጥሊያ

29. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ጉልበት ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ጉልበት ስራን የመስራት አቅም ነው　　ለ. ጉልበት እና ሀይል አንድ ናቸው

ሐ. ጉልበት ይዘት እና መጠነ-ቁስ አለው　　መ. ጉልበት አንድን ቁስ መግፋት ወይም መጎተት ነው

30. ከሚከተሉት ውስጥ የቀላል መኪና አላማ **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. ፍጥነትን መጨመር　　ለ. የኃይልን አቅጣጫ ማስቀየር

ሐ. ጉልበትን ያበዛል　　መ. ኃይል ይጨምራል

31. ከሚከተሉት ውስጥ ነገሮችን አጥብቆ ለማሰር እና ጠንካራ የሆኑ ነገሮችን ለመሰርሰር የሚጠቅም ቀላል የመኪና አይነትየቱ ነው?

ሀ. መፈንቅል　　ለ. መፍቻ　　ሐ. ሽብልቅ　　መ. ሽክርክሪት



LIVEWORKSHEETS

32. ከሚከተሉት ውስጥ ከምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀገራት መካከል በአንዳንድ የኢትዮጲያ፣ የኬንያ እና የታንዛንያ ቦታዎች ዝቅተኛ ሙቀት ሊኖራቸው የቻለበት ምክንያትን የቱ ነው?

ሀ. በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ስለሚገኙ ለ. ከምድር ወገብ ርቀው ስለሚገኙ

ሐ. ከባህር ባላቸው ርቀት ምክንያት መ. በከፍተኛ ቦታዎች ስለሚገኙ

33. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ በምድር ወገብ አካባቢ የሚገኙ ሀገራት ከፍተኛ ሙቀት የሚያገኙበት ምክንያትን የያዘው የቱ ነው?

ሀ. የፀሀይ ጨረር በቀጥታ ስለሚያርፍባቸው ለ. የፀሀያ ጨረር በሰያፍ ስለሚያርፍባችው

ሐ. በሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ስለሚገኙ መ. በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ስለሚገኙ

34. ከሚከተሉት ውስጥ በምስራቅ አፍሪካ ሰሜናዊ ክልል የሚገኙ ብዙ አካባቢዎች ዝናብ የሚያገኙት በየትኞቹ ወራት ነው?

ሀ. ከታህሳስ እስከ የካቲት ለ. በጥቅምት እና በሚያዚያ

ሐ. ከሰኔ እስከ መስከረም መ. በህዳር እና በመጋቢት

35. ከሚከተሉት የአየር ንብረት ክልሎች ውስጥ ዝቅተኛ ሙቀት የሚመዘገብበት የቱ ነው?

ሀ. የሳር ምድር የአየር ንብረት ለ. የደጋ የአየር ንብረት

ሐ. የሐሩር የባህር ዳርቻ የአየር ንብረት መ. የበረሀ የአየር ንብረት

36. ከሚከተሉት ሀገሮች ውስጥ የወርቅ፣ የብር እና የበረት ማዕድናት የሚገኝበት ሀገር የተኛው ነው?

ሀ. ዩጋንዳ ለ. ሶማሊያ ሐ. ሞዛምቢክ መ. ኢትዮጲያ



LIVEWORKSHEETS

37. ከሚከተሉት የተፈጥሮ ሀብት አተቃቀም ዘዴዎች ውስጥ ተገቢ **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. የአፈርን መሸርሸር ለመከላከል ዛፍ መትከል

ለ. የፋብሪካ ተረፈምርት ቆሻሻዎችን ከወንዝ ጋር ማያያዝ

ሐ. የተፈጠሮ ሀብት አያያዝ ሕጎችን ማክበር መተግበር

መ. እንደ ንፋስ እና ፀሀይ ያሉ የኃይል አማራጮችን መጠቀም

38. ከሚከተሉት ውስጥ በኢትዮጲያ **የማይገኘው** የአፈር አይነት የቱ ነው?

ሀ. ቨርቲሶል ለ. ካምቢሶል ሐ. ዜሮሶል መ. ላቪሶል

39. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ ማዕድን ጠቀሜታ **የማይገልፀው** የቱነው?

ሀ. የስራ እድል አይፈጥርም

ለ. የገቢ ምንጭን ለማሳደግ

ሐ. የገበያ ትስስር ለማሳደግ

መ. ለውጭ ምንዛሪ ምንጭነት

40. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ የማዕድን አጠቃቀም ተግዳሮት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የሀገር ውስጥ ፍላጎት መጨመር

ለ. ዝቅተኛ መሰረተ ልማት

ሐ. የማዕድን ቁፋሮ ባለሙያ መኖሩ

መ. የቴክኖሎጂ መስፋፋ



LIVEWORKSHEETS

LIVEWORKSHEETS